# በኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለስልጣን

## የ1984ዓ፡ የስታቲስቲክስ ሥራ እቅድ

መጋቢት 1983
አዲስ አበባ

# ማውጫ


ገጽ

1. መግቢያ ........................................ 1
2. የ1983 የስታቲስቲክስ እቅድ አፈጻጸም ግምገማ .................. 2
3. የ1984 የስታቲክስ ሥራ እቅድ ዓላማዎች፣ ስልቶችና ግቦች .................................... 18
4. የ1984 የስታቲስቲክስ እቅድ ይዘት .......................... 23
5. የ1984 የገንዘብና የማቴሪያል ፍላጎት .......................... 51
6. የሰው ኃይል ፍላጎት .................................. 52
7. መወሰድ የሚኖርባቸው የፖሊሲና ድርጅታዊ እርምጃዎች .............. 53

# የ1984 የስታቲስቲክስ ሥራ ዕቅድ

## 1. መግቢያ ፤

የአገሪቱን የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ግንባታ በተገቢው መንገድ ለማራመድና ለማፋጠን ተጨባጭ ሁኔታዎች በሚፈቅዱት መሠረት የአጭር ፤ የመካከለኛና የረዥም ጊዜ ዕቅዶች ገቢ እንዲሆኑ ለማድረግ የማዕከላዊ ፕላንን እንደ ዓይነተኛ መሣሪያ ተወስዶ ሲሠራበት ቆይቷል::

ማዕከላዊ ፕላንን ተግባራዊ በማድረግ ረገድ የፕላን መዋቅር በአገሪቱ በሰፋት በመዘርጋት በየማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዘርፎች የፕላን አሠራር እንዲስፋፋና ልምዱም ደረጃ በደረጃ እየጐለበተ እንዲሄድ አመቺ ሁኔታዎች ተፈጥረዋል:: ለኢኮኖሚና ማሕበራዊ ፕላን ተግባራዊነት ደግሞ ስታቲስቲካዊ መረጃዎች በቅድሚያ በየዘርፉ መገኘት ወሣኝነት አለው:: በተለይም ለዕቅድ ዝግጅት ፤ የልማት ፖሊሲዎችንና ፕሮግራሞችን ለመቀየስ ፤ እንዲሁም ምርምሮችንና ሌሎች ተመሳሳይ ተግባራትን ለማከናወን በየክፍለተ ኢኮኖሚው ተጨባጩን ሁኔታ ሊገልጽ የሚችል ወቅታዊ ፤ የተሟላና አስተማማኝ የሆነ ስታቲስቲካዊ መረጃ ጠቃሚነቱ ከፍተኛና ወሣኝ እንደሆነ ይታመናል::

ስለሆነም የአገሪቷን የስታቲስቲክስ መረጃ ፍላጐት በማሟላት ረገድ የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን ከፍተኛ ተግባርና ኃላፊነት የተጣለበት በመሆኑ ባለሥልጣኑ ለብሔራዊ ስታቲስቲክስ ሥራ ዕድገት አመቺ ሁኔታዎችን በመፍጠር ፤ በየጊዜው የተሻለ የአሠራር ዘዴዎችን በመቀየስ ተግባር ላይ እንዲውሉ ጥረት በማድረግና እንዲሁም የአገሪቷን የዕድገት አቅጣጫና የአቅም ሁኔታዎችን በማገናዘብ ልዩ ልዩ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሁኔታዎችን የሚገልጹ ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን ለማስገኘት የተቻለውን ሁሉ ሲያከናውን ቆይቷል:: አሁንም በማከናወን ላይ ይገኛል::

ባለሥልጣኑ ይህን የሚጠበቅበትን ተግባርና ኃላፊነት ለመወጣት የሚያስችለውን ዕቅድና ፕሮግራም በማዘጋጀት ተግባር ላይ ያውላል:: ከዚሁ አኳያ ከዚህ በፊት የቀረቡትን የስታቲስቲክስ ዕቅድ ዓላማዎችና ስልቶች መሠረት በማድረግ የ1984 የስታቲስቲክስ ዕቅድ ተዘጋጅቷል::

የዕቅዱም አዘገጃጀት እስከዛሬ የተገኘውን ልምድ በመገምገም ፤ አገሪቷ ያለችበትን ሁኔታ በማጤንና ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ ጥናቶችንና ሥራዎችን በማገናዘብ ሲሆን ፤ የ1983 የዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ ፤ የ1984 የስታቲስቲክስ ዕቅድ ዓላማዎች ፤ ስልቶችና ግቦች ፤ የዕቅዱ ይዘት ፤ የገንዘብ፤ የማቴሪያልና የሰው ኃይል ፍላጐት እንዲሁም በአጋጠሙ ችግሮች ላይ መወሰድ የሚኖርባቸው እርምጃዎችንም የሚያጠቃልል ይሆናል::

.../ 2

እንደዚሁም የአዲስ አበባና የአሥመራ መረጃ የስድስቱም ወራት በየ ወቅቱ ተሰብስቧል::

2.2 <u>ከተለያዩ ጥናቶች የተሰበሰቡትን መረጃዎች አቀነባብሮ ውጤቱን በሪፖርት መልክ ማውጣትና ከዚሁ ጋር ተመሳሳይነት ያላቸውን ሌሎች ሥራዎች ማከናወን በተመለከተ የተከናወነ ፤</u>

2.2.1 <u>የግብርና ስታቲስቲክስ ጥናቶች ፤</u>

2.2.1.1 የ1981 የግብርና ናሙና ጥናት አጠቃላይ መረጃ/የግል የመንግሥትና የሕብረት እርሻዎች/ የያዘ ሪፖርት ተዘጋጅቶ ለተጠቃሚዎች ተሠራጭቷል::

2.2.1.2 የ1979 እና የ1980 የቤት እንስሳት ብዛት በዓይነት ፤ በፆታና በዕድሜ /ለገጠሬ ፤ ለአምራቾችና ለመንግሥት/ የያዘ ሪፖርት በአንድ ጥራዝ ተዘጋጅቶ ለተጠቃሚዎች የተሰራጨ ሲሆን የዚሁ ጥናት የ1981 ሪፖርት ዝግጅት ተጠናቆ በሕትመት ላይ ይገኛል::

2.2.1.3 የ1982 አጠቃላይ ሪፖርት ዝግጅት የሚሆነው የ1982 የአምራቾች የበልግ ወቅት መረጃና የመንግሥት እርሻዎች የዓናው መኸር በመምሪያው ባለሙያዎች በፒሲ ተቀነባብሯል::

2.2.1.4 የ1982 የቤት እንስሳት የገጠሬ ባለይዞታዎች መረጃ የኮምፒዩተሩ ከዳንገና የመረጃ ማጥራት ሥራ ተጠናቆ ሪፖርቱ በቅርቡ እንደሚወጣ ይጠበቃል:: እንደዚሁም የዚሁ ጥናት የ1982 የመንግሥት እርሻን በተመለከተ ውጤቱ በመቀነባበር ላይ ይገኛል::

2.2.1.5 በ FOOD INFORMATION SYSTEM ፕሮጀክት አማካይነት ከተለያዩ መ/ቤቶች የሚሰበሰበው መረጃ የቀጠለ ሲሆን በሰብል ትንበያ ጥናት የሚሰበሰበውን " የሰብል ሁኔታ " መረጃ በመጠቀም ሪፖርቱ በኅዳር ወር 1983 ተዘጋጅቶ ለተጠቃሚዎች ተሠራጭቷል::

2.2.3 <u>ዓመታዊ የትራንስፖርትና መገናኛ መጽሔት ፤</u>

ለ1980 የትራንስፖርትና መገናኛ መጽሔት ዝግጅት የተሰበሰበው መረጃ ሪፖርት ተጠናቆ ለተጠቃሚዎች ተሠራጭቷል:: የዚሁ ጥናት የ1981 መረጃም የአርምት ሥራ ተጠናቆ በመቀነባበር ላይ ይገኛል::

2.2.4 <u>የአምራቾችና የቸርቻሮ ዋጋዎች ጥናት ፤</u>

2.2.4.1 የአዲስ አበባ የቸርቻሮ ዋጋ መመዘኛ ኢንዴክስ ሥራ ጠቅላላ ጠብቆ በየወሩ እየተዘጋጀ ለተጠቃሚዎች እንዲሠራጭ ተደርጓል::

2.2.4.2 <u>በገጠር የአምራችና የቸርቻሮ ዋጋዎች ጥናት ፤</u>

የዚህ ጥናት የ1980 መረጃ የዳታ ኢንትሪና የኮምፒዩተር ቀን ብር ሥራ ተጠናቆ የሪፖርት ዝግጅት ከተጀመረ በኋላ በአምራች ዋጋ መረጃ ላይ ስህተት በመታየቱ ታርሞና ተስተካክሎ ሪፖርቱ በሕትመት ላይ ይገኛል:: የ1981 የአምራች ዋጋ መረጃ ለመጠረሻው ሪፖርት ዝግጅት የኮምፒዩተር ቀንብሩ ተግባር የቀጠለ ሲሆን የቸርቻሮ ዋጋ መረጃም የዳታ ኢንትሪ ሥራ ተጠናቆ ፀአርምት ላይ ይገኛል::
እንደዚሁም የዚህ ጥናት የ1982 መረጃ እስከ መጋቢት ወር ድረስ የኤዲቲንግ ፣ የኮዲንግና የዳታ ኢንትሪ ሥራ ተጠናቋል::

2.2.4.3 የ1981/82 የ23 ከተሞች የቸርቻሮ ዋጋዎች ጥናት ሪፖርት ዝግጅት ተጠናቆ በሕትመት ላይ የሚገኝ ሲሆን የ1982 መረጃም በኮምፒዩተር የማቀነባበሩ ተግባር ቀጥሏል::

2.2.4.4 በተመረጡ 23 ከተሞች የማኮሃርጣ የሆቴሎች ፣ የአልጋና የምግብ ዋጋ ጥናት የ1981/82 መረጃ ሪፖርት በሕትመት ላይ የሚገኝ ሲሆን የ1982 በጀት ዓመት መረጃ ደግሞ በኮምፒዩተር የማቀነባበሩ ተግባር ተጠናቆ ሪፖርት ለማዘጋጀት ሥራ ተዘጋጅቷል::

2.2.5.5 የቤተሰብና የወሊድ ሁኔታን ጥናት በአገር አቀፍ ደረጃ /ኤርትራ ትግራይ ፣ ጐንደር ፣ ወሎን ሳይጨምር/ የመረጃ አሰባሰቡ ተግባር በሐምሌ ወር 1982 መጨረሻ የተጠናቀቀ ሲሆን በጥናቱ የተሞሉ መጠይቆችም ወደ ዋናው መ/ቤት ተጠቃለው ገብተዋል::

ለዚሁም መረጃ ቀንበር የኤዲቲንግና ኮዲንግ መመሪያ ተዘጋጅቶ ሥራው በመከናወን ላይ ይገኛል:: ይኸውም በማጠቃለያ ቅጾች የተሞሉት መረጃዎች በኮምፒዩተር የተቀረጹ ሲሆን የመረጃዎች ማገናዘብ/Consistency Check/ የማድረግ ተግባር ተከናውኗል::

2.2.6 <u>በገጠር የአመጋገብ ጥናት ፣</u>

በ1974/75 በገጠር የተካሄደውን የአመጋገብ ጥናት ውጤት የያዘ ሪፖርት ተዘጋጅቶ ቀደም ሲል ለተጠቃሚዎች የተሠራጨ ሲሆን በዚሁ ጥናት በተካሄዱት ሦስት ዙሮች በመጨረሻዎቹ ሁለት ዙሮች ስለተሰበሰቡት የሕጻናት አመጋገብ ሁኔታን የሚያመለክቱ መረጃዎች የተንተና ሪፖርት ዝግጅት ረቂቅ ተጠናቋል::

2.2.7 <u>ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት ፣</u>

የ1979 እና የ1980 እንዲሁም አለፍ አለፍ የ1981 መረጃዎችን የያዘ ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት ዝግጅትን በተመለከተ የቀንበሩና የመተየቡ ተግባር ተጠናቆ በሕትመት ላይ ይገኛል:: እንዲሁም በዓይነታቸውና በመጠናቸው የተመረጡ አጠቃላይ መረጃዎችን ብቻ የሚይዝ አነስተኛ መጽሔት ተዘጋጅቶ ለተጠቃሚዎች ተሠራጭቷል::

2.2.8 <u>ሌሎች የተከናወኑ ተግባራት ፣</u>

2.2.8.1 ለልዩ ልዩ መ/ቤቶችና ድርጅቶች አስፈላጊው የቴክኒክ የማቴሪያል እርዳታ ተደርጓል::

2.2.8.2 ለቤተሰብና ወሊድ ጥናት ውጤት ቀንበር የሚረዳ በገጠርና በከተማ የሚገኙትን ቀበሌዎች በየአስተዳደር አካባቢና በአውራጃ የሚያሳይ መለያ ኮድ ተዘጋጅቷል:: ለዚሁ ጥናት ውጤት ማባዣ/መልቲፕላየር/ የተዘጋጀ ሲሆን የሚቶደሉኚ ሪፖርት ዝግጅትም በመጠናቀቅ ላይ ነው::

[illegible] ፳ ማቋቋሚያ ኰሚሽን ለቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ጥናት ሥራ ማስኬጃ ብር 50,000 ነው::

2.3.2 የሰው ኃይል አጠቃቀም ፤

በዕቅድ ዓመቱ መጀመሪያና በሁለተኛው ሩብ ዓመት መጨረሻ የነበረው የሰው ኃይል ብዛት ቀጥሎ በሠንጠረዥ ቀርቧል::

የሰው ኃይል በቅጥር ዓይነት

| አጠቃላይ ሁኔታ | የሠራተኛ ቅጥር ሁኔታ | | ጠቅላላ |
|---|---|---|---|
| | ቋሚ | ኰንትራት | ድምር |
| በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ የነበረ | 403 | 1394 | 1797 |
| አዲስ የተቀጠረ | 19 | 36 | 55 |
| ከሥራ የተሰናበተ | 13 | 11 | 24 |
| ታህሣሥ 30/1983 የነበረ | 409 | 1419 | 1828 |

ከዚህ በላይ በቀረበው ሠንጠረዥ እንደሚታየው 409 ቋሚና 1419 የኰንትራት በድምሩ 1828 ሠራተኞች ይገኛሉ:: ይህም ከዕቅድ ዓመቱ መጀመሪያ ከነበረው የሰውኃይል ጋር ሲነፃፀር 1 7% ዕድገት አሣይቷል:: እንደዚሁም 24% የሚሆኑት ቋሚ ሠራተኞችና 92% የሚሆኑት የኰንትራት ሠራተኞች ማለትም 1308 መረጃ ሰብሳቢዎች ፤ ረዳት ተቆጣጣሪዎችና ፤ ሾፌሮች ከአዲስ አበባ ውጪ በየአስተዳደር አካባቢው ተመድበው በመሥራት ላይ ይገኛሉ:: በተጨማሪም የሠራተኞች ብዛት በጾታ ተለይቶ ሲታይ 336 ወንድና 73 ሴት ቋሚ ሠራተኞች ሲሆኑ 1198 ወንድና 221 ሴት የኰንትራት ሠራተኞች ናቸው::

ስለጊዜያዊ ሠራተኞች የአቀጣጠር ሁኔታን በተመለከተ ፤ በተመረጡ ገበሬ ማህበራት የግብርና ጥናት በተለይም የሰብል አጨዳና የታረሰ መሬት ልኬት በሚከናወንበት ወቅት ለእያንዳንዱ መረጃ ሰብሳቢ ረዳት ስለሚያስፈልገው ለሁለት ወራት ገደማ ጊዜያዊ ሠራተኞች በቀን ሙያተኛነት ይቀጠራሉ::

እንደዚሁም ለተወሰኑ ጥናቶችና ሥራዎች ጊዜያዊ የሥራ ውጥረት በሚኖርበት ወቅት ብቻ የጉልበት ሠራተኞች እንደሚቀጠሩ መታወቅ ይኖርበታል።

## 2.4 ያጋጠሙ ችግሮች ፤

ባለፉት የዐቅድ ዐመታት በቀረቡት የዐቅድ አፈጻጸም ሪፖርቶች ውስጥ መሥሪያ ቤቱን ያጋጠሙ ዋና ዋና ችግሮች መቅረባቸው አይዘነጋም። እነዚህ ችግሮች እስከዛሬ መፍትሔ ያላገኙ በመሆናቸው አሁንም በመሥሪያ ቤቱ ሥራ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ በማድረግ ላይ ናቸው። ስለሆነም በዚህም ሪፖርት በተመሳሳይ ሁኔታ ዋና ዋናዎቹ ችግሮች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

### 2.4.1 የቢሮ ጥበት ፤

የሀገርን እድገትና ልማት ለማፋጠን በማዕከላዊነት በየጊዜው የሚወጡትን ዕቅዶች ለማስፈጸም በሚደረገው የሥራ እንቅስቃሴ በብዛት እያደገ የመጣውን ሥራና የሰው ኃይል በተወሰኑ ቢሮዎችና የቦታ ይዞታ ለማስተናገድ ካለመቻሉም በላይ ሥራዎችን በሚፈለገው መንገድና ዓይነት ለማከናወን ከባድ ችግር እየፈጠረ ነው።

ይህም የመሥሪያ ቤቱ ቋሚ ችግር ሆኖ የቆየው የቢሮ ጥበት ሁኔታ መፍትሔ እንዲያገኝ በ1980 የበጀት ዓመት ለሕንጻ ዲዛይን ሥራ በጀት ተፈቅዶ የመጨረሻ ደረጃ የዲዛይን ሥራ የተጠናቀቀ ቢሆንም በልዩ ልዩ ምክንያቶች የሕንጻው ሥራ በታሰበው ወቅት ባለመጀመሩና የተጨማሪ ሠራተኞች በብዛት መመደብ ችግሩን ስላባባሰው አነስተኛ ቢሮዎች በመቀጣጠልና በመከፋፈል ለማቃለል ቢሞከርም እርምጃው ዘላቂና አጥጋቢ መፍትሄ ሊሆን አልቻለም።

### 2.4.2 የመሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ትብብር ማነስ ፤

ለስታቲስቲክስ መረጃዎች በወቅቱና በጥራቱ መገኘት የመሥሪያ ቤቶች ፣ የድርጅቶችና የግለሰቦች ትብብር በከፍተኛ ደረጃ የሚጠበቅ ነው። ይሁን እንጂ ባለፉት ዓመታት እንደታየው ሁሉ በዚህም የዐቅድ ዓመት የተሳትፎም ሆነ የትብብር ሁኔታ ዝቅተኛ ሆኖ ተገኝቷል።

እንደዚሁም የተለያዩ ገለሰቦች በኃላፊነት ካንቀሳቀሱት ገንዘብ በጉድለት የሚፈለግባቸው የሰነድ ሂሣብ መ/ቤተ በተመሣሣይ ሁኔታ በዐዓ በየጊዜው ይጠየቅበታል::

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው በኘሮጀክቶች ሥራ ማስኬጃ በልዩ ልዩ አርዕስት የተፈቀደው በጀት በየወሩ ሲጠየቅ እየተቀነሰ ስለ ሚከፈል በሥራ አፈጻጸም ላይ ችግር አስከትሏል:: ሆኖም በኘር ግራሙ መሠረት የተፈቀደው በጀት ዘግይቶም ቢሆን ተሟልቶ ይሰጣል በሚል ግምት በመ/ቤቱ ካዝና ከሚገኝ ማናቸውም ገንዘብ ላይ ክፍያ እንዲፈጸም ሁኔታው ያስገድዳል:: በመጨረሻም በወጪ አርእስት ለማስተካከል ለበጀት ዓመቱ የተፈቀደው ገንዘብ ሲጠየቅ ክፍያው የተፈጸመው ለአርዕስቱ ከተያዘው የበጀት ጣሪያ በላይ ያለመሆኑ እየታወቀ ከገንዘብ ሚኒስቴር ተጠይቆ ከመጣው በላይ ተከፍሏል እየተባለ በየዓመቱ ፊሰስ እንጠየቅበታለን:: ችግሩም ከዘመን ወደ ዘመን እየተሸጋገረና እየተደራረበ በየዓመቱ አዳዲስ የፊሰስ ዕዳ እየታከለበተ በመሄዱ አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደርሷል::

.../፲፰

የስታቲስቲክስ ሥራ እቅዱ ተዘጋጅቷል:: በእቅዱ የተያዙት ጥናቶች ገጠርና ከተማን የሚሸፍን ሲሆን ከመዛግብት የሚሰበሰቡት መረጃዎችም ወደፊት አቅም በፈቀደ መጠን በዓይነትም ሆነ በብዛት እየጨመረ እንደሚሄዱ ታሳቢ ሲደረግ ፣ የአምስት ዓመት እቅዱ አካል በሆነው በ1984 የሚካሄዱ ዝርዝር ጥናት ዓይነቶችና ሌሎች ሥራዎች ተለይተው ከዚህ በታች ቀርበዋል::

4. <u>የ1984 የስታቲስቲክስ እቅድ ይዘት ፣</u>

በ1984 ለማካሄድ የታቀዱት የስታቲስቲክስ ሥራዎች ሦስት ዋና ዋና ይዘት ያላቸው ሲሆኑ እነሱም:-

4.1 የተለያዩ ጥናቶችን ማካሄድ ፣

4.2 ከተለያዩ ጥናቶች የተሰበሰቡትን መረጃዎች አቀናብሮ ውጤትን በሪፖርት መልክ ማውጣትና ከዚህ ጋር ተመሳሳይነት ያላቸውን ሌሎች ሥራዎች ማከናወን ፣

4.3 በተከታዩ ዓመት ይከናወናሉ ተብሎ ለሚታሰቡ ጥናቶችና ሥራዎች አስፈላጊውን ዝግጅት ማድረግ ናቸው::

4.1 <u>የተለያዩ ጥናቶችን ማካሄድ በተመለከተ ፣</u>

በ1984 ስታቲስቲካዊ ጥናቶችን በማካሄድ ልዩ ልዩ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ መረጃዎችን ለመሰብሰብ በእቅድ የተያዙት የጥናት ዓይነቶች ፣ የጥናቶች ዝርዝር ዓላማና የሚሰበሰቡት ዋና ዋና መረጃዎች ቀጥሎ በዝርዝር የተመለከቱት ናቸው::

<u>የጥናቶቹ ዓይነቶች ፣</u>

- የሰብል ትንበያ ጥናት ፣
- የእርሻ ናሙና ጥናት ፣
- የሕብረት እርሻዎች ጥናት ፣
- የመንግሥት እርሻዎች ጥናት ፣
- የአነስተኛ ሥራ ሥር ተከሎች ጥናት ፣
- የማምረቻና የኤሌክትሪክ ኢንዱስትሪዎች ጥናት ፣
- የሕንፃ ኮንስትራክሽን ጥናት ፣
- የማዕድን ስታቲስቲክስ ጥናት ፣
- የአነስተኛ ዕደ - ጥበብ ኢንዱስትሪዎች ጥናት ፣

በዚህ ጥናት የሚሰበሰቡት የመረጃ ዓይነቶች ዝርዝርም ፤

— እድሜ ፣ጾታ ፣ የትምህርት ሁኔታ ፣ ብሔረሰብና ሃይማኖት ፣

— የእርሻ ይዞታና የቤተሰቡ የምርት ዓይነት ፤

— የተለያዩ ዕቃዎች በቤተሰቡ መገኘት ፤

— የሥራ ዓይነቶች ዝርዝርና በሥራ ላይ የጠፋ ሰዓት ፣

— ስለአካባቢው ማህበራዊና ባህላዊ ሥነ ሥርዓቶች

— የጤናና ሌሎች መሠረታዊ የአገልርሎት ተቋሞች መኖር ፣

— ስለአዛውንቶች እንክብካቤ ፣ ስለቤተሰቡ አባላት ብዛትና የመረ ዳት ሁኔታዎች ፣

<u>የጤና ጥናት /በገጠር/ ፤</u>

ይህ ጥናት በከተማና በገጠር የሚካሄድ ሲሆን ዓላማውም ስለሕዝቡ የጤና ሁኔታዎችን እንደዚሁም ከእነዚህ ጋር የሚዛመዱትን ሌሎች ሁኔታዎችን የሚያመለክቱ መረጃዎችን ለማስገኘት ነው:: የመረጃዎቹም ውጤት የሕዝቡን የጤንነት ሁኔታ ለማሻሻል ለሚዘጋጁ እቅዶችና ለሚቀየሱ ፖሊሲዎች መሠረት በመሆን ያገለግላል::

በጤና ጥናት የሚሰበሰቡት የመረጃዎች ዓይነት/—

— የማህበራዊና የሥነ — ሕዝብ ባህርያት ፣

— ስለሕመም ሁኔታ ፣

— ስለ አደጋዎችና መንስዔዎቻቸው ፣

— በበሽታ ወይም በአደጋ ምክንያት የዘወትር ተግባርን ስለማቋረጥ

— በበሽታ ወይም በአደጋ ምክንያት የደረሰ ጉዳት በግለሰቦች ላይ የቆየበት የቀናት ብዛት ፣

— ስለ ሕክምና መሻትና ማግኘት ፣

— ስለ ነፍሰጡር ሴቶች ጤና አጠባበቅ ፣

— እናቶች ሲወልዱ ስለሚጠቀሙባቸው የማዋለጃ ግልጋሎቶች

— የንጽህና መገልገያዎች ስለመኖራቸው ፤

— የእናቶችና የህጻናት ክትባት ፣

— የንጽህና መገልገያዎች ስለመኖራቸው

4.3.2 በ1985 ሊካሄዱ ለታቀዱ አዳዲስና በቋሚነት ለሚካሄዱ ጥናቶች አስፈላጊ የሆኑ ቅጾችን መጠይቆችን ፣ መመሪያዎችን የመስክ መገልገያ መሣሪያዎችንና ሌሎች የጥናት ዶኩመንቶችን ማዘጋጀት ፣ በተለይም አጠቃላይ የግብርና ቆጠራን በተመለከተ አስፈላጊ ቅድመ ዝግጅት በሙሉ መጠናቀቅ ይደርበታል::

4.3.3 ለአጠቃላይ የግብርና ቆጠራና ለሌሎች ጥናቶች አስፈላጊ የሆኑ የቴክኒክ ማቴሪያሎች የሚገኙበትንና የሚሟሉበትን መንገድ በመቀየስ ተግባራዊ ማድረግ ፣

4.3.4 በግብርና ቆጠራና በሌሎች ጥናቶች ላይ የሚሳተፉትን መረጃ ሰብሳቢዎችና ሌሎች ባለሙያዎችን ብዛትና የሚገኙበትን ሁኔታ መወሰን ፣ ስለምልመላና ሥልጠና ዝግጅት ማጠናቀቅ::

በ1984 ከሚካሄዱት ሥራዎች መካከል በተለያዩ ምክንያቶች ሲሸጋሸግ ለቆየው አጠቃላይ የግብርና ቆጠራ የቅድመ ዝግጅት ሥራ ማጠናቀቅ አንዱ መሆኑ ተጠቅሷል:: የዚህ ቆጠራ ዋና ዓላማ በዚህ ክፍለ ኢኮኖሚ ለሚደረገው የልማት እቅድና ዝግጅት ፣ እንዲሁም ለፖሊሲ ውሳኔ አሰጣጥ መሠረት በመሆን ሊያገለግሉ የሚችሉ ወቅታዊ የሆኑ የግብርና መረጃዎችን ሰፋ ባለ ሁኔታ ለማስገኘት ነው:: መሠረታዊ የሆነ የግብርና መረጃ መኖር የምግብ አቅርቦትን ለማሻሻል የእንስሳት ሀብትን ብዛትና ዓይነት ለመገምገም ፣ ለኢንዱስትሪዎች የሚያስፈልጉትን የጥሬ ዕቃ አቅርቦትን ለማሻሻልና በክፍለ ኢኮኖሚው ቁጥጥርና ክትትል ለማድረግ የሚያስችል መሆኑ ከሚያበረክተው አስተዋጽኦ መጠቀስ ከሚገባቸው ነገሮች ናቸው::

ቆጠራው የሚካሄደው የወቅቱ ሁኔታ በፈቀደው መጠን የአገሪቱን የአስተዳደር ክልል በሙሉ እንደሚሸፍንና ከአውራጃ ጀምሮ ባሉት የአስተዳደር ደረጃዎች መረጃውን ለማቅረብ እንደሚያስችል ታስቧል:: የዚህ ቆጠራ እውን መሆን በዝቅተኛ የአስተዳደር ክልል ጭምር በከፍተኛ ደረጃ እየጨመረ የመጣውን የግብርና ነክ መረጃ ፍላጎት እንደሚያሟላ ይታመናል::

በዚህ ቆጠራ የሚሰበሰቡ የመረጃ ዓይነቶች የሚከተሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው:-

- የባለይዞታዎች የሥነ ሕዝብ ባሕርያት ፣
- የግብርና ዓይነት ፣
- የመሬት አጠቃቀም ፣
- የመስኖ ዘዴ ስለመጠቀም ፣
- የእርሻ መሣሪያዎች ዓይነትና ብዛት ፣
- ስለ ዘር ዓይነትና የአጨዳ ወቅት ፣
- በሰብል ዘመኑ የታረሰ መሬት ስፋትና የምርትን መጠን በሰብል ዓይነት ፣
- ስለ ምርት አጠቃቀም /ዘር፣ ፍጆታ፣ ሽያጭ ... ወዘተ ፣
- ጥቅም ላይ የዋለ የማዳበሪያ ዓይነትና መጠን ፣
- ፀረ-ሰብል ተባይ ማጥፊያ መድኃኒት ስለመጠቀም ፣
- የቤት እንስሳት ብዛት በዓይነት ፣ በዕድሜና በጾታ ::

4.3.5 ለስታቲስቲክስ መዝገብ አያያዝ የሙከራ ጥናት አስፈላጊውን የቀደመ ዝግጅት ሥራዎች ማጠናቀቅ ፣ ይህ ጥናት በተለያየ ምክንያት ሲሸጋሸግ የቆየ መሆኑ ቢታወቅም በተወሰኑ የኢኮኖሚ ዘርፎች የሙከራ ጥናት ለማካሄድ በቀዳሚያ ስለሥራው ይዘትና ዝርዝር የአሠራር ሁኔታዎችን ለማዘጋጀት በዚህ መስክ ባለሙያዎችን ማሠልጠን ወይም በቂ ልምድ ካላቸው አገሮች ልምድ ማግኘት አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበታል:: ስለዚህ በተወሰኑ የኢኮኖሚ ዘርፎች ይህን ጥናት ለማስጀመር የባለሙያዎች ሥልጠና ወይም ልምድ ማግኘት ወሳኝነት ስላለው በ1984 የእቅድ ዓመት አስፈላጊው ጥረት ይደረጋል::

... /- 39

## 4.4 የ1984 እቅድ ዝርዝር የሥራ ፕሮግራም፣

ባለሥልጣኑ የሚያከናውናቸው አበይት ተግባራት ሦስት ዓይነት ይዘት እንዳላቸው ቀደም ሲል ተጠቅሷል:: ይኸውም የተለያዩ ጥናቶችን በማካሄድ ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን መሰብሰብ፣ የተሰበሰቡ መረጃዎችን አቀነባበር በሪፖርት መልክ ማውጣትና ተመሳሳይነት ያላቸው ሥራዎችን ማከናወን፣ እንዲሁም በተከታዩ ዓመት ይከናወናሉ ተብሎ ለታሰቡ ጥናቶች ሥራዎች አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት ማድረግ ናቸው::

የእነዚህ አበይት ተግባራት ዝርዝርና የአፈጻጸም ሁኔታ በየሩብ ዓመት እንደሚከተለው ቀርቧል::

መግለጫ፣ 1ኛ ሩብ ዓመት – ከሐምሌ 1 ቀን 1983 እስከ መስከረም 30 ቀን 1984

2ኛ ሩብ ዓመት – ከጥቅምት 1 ቀን 1984 እስከ ታህሣሥ 30 ቀን 1984

3ኛ ሩብ ዓመት – ከጥር 1 ቀን 1984 እስከ መጋቢት 30 ቀን 1984

4ኛ ሩብ ዓመት – ከሚያዝያ 1 ቀን 1984 እስከ ሰኔ 30 ቀን 1984

" – " በተጠቀሰው ሩብ ዓመት ጥናቱ ወይም ሥራው ያለማቋረጥ በተከታታይ የሚሠራ መሆኑን ያመለክታል::

" × " በተጠቀሰው ሩብ ዓመት ጥናቱ ወይም ሥራው ለተወሰኑ ቀናት ብቻ የሚሠራ መሆኑን ያመለክታል::

## 4.4.1 ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን ለማስገኘት የተለያዩ ጥናቶችን ማካሄድ በሚመለከት ፤

| ተራ ቁጥር | የ ጥ ና ቱ ዓ ይ ነ ት | ጥ ና ቱ የ ሚ ካ ሄ ድ በ ት ጊ ዜ | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት |
| 1 | የሰብል ትንበያ ጥናት ፤ | — | | | |
| 2 | የእርሻ ናሙና ጥናት ፤ | — | — | — | |
| 3 | የሕብረት እርሻዎች ጥናት | — | — | — | — |
| 4 | የመንግሥት እርሻዎች ጥናት | | | — | — |
| 5 | የእንስትና ሥራ ሥር ተክሎች ጥናት ፤ | — | — | | |
| 6 | የማምረቻና ኤሌክትሪክ ኢንዱስትሪዎች ጥናት | — | | | |
| 7 | የሕንፃ ኮንስትራክሽን ጥናት ፤ | | — | — | |
| 8 | የማዕድን ስታቲስቲክስ ጥናት ፤ | — | — | | |
| 9 | የአነስተኛ ዕደ ጥበብ ኢንዱስትሪዎች ጥናት ፤ | | | — | — |
| 10 | የውጭ ንግድ ፤ ትራንስፖርት ፤ መገናኛና ፋይናንስ ጥናት፤ | — | — | — | — |
| 11 | የዋጋዎች ጥናት ፤ | | | | |
| | — የአምራችና የችርቻሮ ዋጋ ጥናት/በገጠር/ ፤ | × | × | × | × |
| | — በ23 ከተሞች የዕቃዎችና የአገልግሎቶች — እንደዚሁም የሆቴሎች ፤ የአልጋና የምግብ ዋጋዎች ጥናት ፤ | × | × | × | × |
| | — በከተሞች የቀድሚያ ማስጠንቀቂያ የዋጋ ጥናት ፤ | × | × | × | × |

4.4.1 /የቀጠለ/

| ተራ ቁጥር | የጥናት ዓይነት | ጥናት የሚካሄድበት ጊዜ | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት |
| 12 | ብሔራዊ የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች | — | — | — | — |
| 13 | የጊዜ አጠቃቀም የሙከራ ጥናት ፡፡ | — | | | |
| 14 | የጤና ጥናት / በገጠር/ ፡፡ | — | × | — | |
| 15 | ብሔራዊ የአመጋገብ ክትትል ሥርዓት ጥናት ፡፡ | — | | — | |
| 16 | የማህበራዊ ጉዳይ ጥናቶች ፡፡ | — | — | — | — |
| 17 | ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት ዝግጅት ፡፡ | — | — | — | — |

### 4.4.2. ከተለያዩ ጥናቶች የሚሰበሰቡትን መረጃዎች አቀነባብሮ ውጤትን በሪፖርት መልክ ማውጣትና ተመሳሳይነት ያላቸውን ሥራዎች ማከናወን በሚመለከት ።

| የጥናቱ ዓይነት | የሥራው ዓይነት | ሥራው የሚከናወንበት ጊዜ | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት |
| የግብርና ስታቲስቲክስ ጥናት | - ሥልጠና ፣ የመስክ ሥምሪት ፣ ክትትልና ቁጥጥር ። | — | | | |
| | - የቅጾችና መመሪያዎች የሕትመት ሥራ ማጠናቀቅና ማሠራጨት ። | — | — | — | |
| | - በሚሰበሰቡት መረጃዎች የኤዲቲንግና ኮዲንግ ሥራ ማከናወን ። | | | | |
| | .ለሰብል ትንበያ ጥናት /1984/ ። | | — | | |
| | .ለእርሻ ናሙና ጥናት ። | | | — | — |
| | .ለሕብረት እርሻዎች ጥናት ። | | | | — |
| | .ለአነስተኛ ሥራ ሥር ተክሎች ጥናት ። | | — | — | |
| | - የሪፖርቶች ዝግጅት ። | | | | |
| | .የ1984 ሰብል ትንበያ ጥናት ። | | — | | |
| | .የ1983 የበልግ ወቅት መረጃ ። | | | — | |
| | .የ1984 የእርሻ ናሙና ጥናት ። | | | | — |

| [illegible] | [illegible] | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት |
|---|---|---|---|---|---|
| የግብርና ስታቲስቲክስ ጥናት | . የ1983 የእርሻ ናሙና ጥናት አጠቃላይ ሪፖርት ዝግጅት | — | — | | |
| | . የእንሰትና ሥራ ሥር ተክሎች ጥናት ። | | | — | |
| | . ሌሎች በ1983 በጀት ዓመት ያልተጠና ቀቁ ሥራዎችና የሌሎች የቴክኒካል ሪፖርቶች ዝግጅት ። | — | — | — | — |
| | . የምግብ መረጃ ሥርዓት/F.I.S/ሪፖርት ዝግጅትና ሥርጭት ። | — | — | — | — |
| የኢንዱስትሪ ስታቲስቲክስ ጥናት | — የ1983 የማዕድን ስታቲስቲክስ መረጃ ማቀነባበርና ሪፖርት ዝግጅት ። | | — | — | |
| | — የ1982 የማምረቻና ኤሌክትሪክ ኢንዱስትሪ መረጃ ማቀነባበርና ሪፖርት ዝግጅት ። | | — | | |
| | — የ1983 የማምረቻና ኤሌክትሪክ ኢንዱስትሪዎች መረጃ አርምት ቀንበርና ሪፖርት ዝግጅት ። | | | — | — |
| | — የአነስተኛና ዐደ ጥበብ ኢንዱስትሪዎች:- | | | | |
| | . መጠይቆች፣መመሪያዎችና የታቡሌሽን ፕሮግራም ዝግጅት ። | — | | | |
| | . የተዘጋጁ መጠይቆችና መመሪያዎች በቴክኒካል ኮሚቴ ማፅደቅ ። | | — | | |

4.4.2 /የቀጠለ/

| የጥናቱ ዓይነት | የሥራው ዓይነት | ሥራው የሚከናወንበት ጊዜ | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት |
| የኢንዱስትሪ ስታቲስቲክስ ጥናት | – የሕንፃና ኮንስትራክሽን መረጃ ቀንበርና ሪፖርት ዝግጅት:– | | | | |
| | • የ1982 መረጃ ቀንበር ። | – | | | |
| | • የ1983 መረጃ ቀንበርና ሪፖርት ዝግጅት ። | | – | – | – |
| የውጭ ንግድ ፣ ትራንስፖርት መገናኛና ፋይናንስ ጥናት | – የ1982 መረጃ ቀንበርና ሪፖርት ዝግጅት | | – | – | – |
| | – የ1983 መረጃ መሰብሰቢያ መጠይቆችን ማዘጋጀትና ማሠራጨት ። | | | | – |
| የዋጋዎች ጥናት ። | – በገጠር የአምራችና የችርቻሮ ዋጋዎችጥናት፡ | | | | |
| | • የ1983 መረጃ ቀንበርና ሪፖርት ዝግጅት | – | – | – | – |
| | • የ1984 መረጃ የኢዲቲንግና ኮዲንግ እንደዚሁም የዳታ ኢንትሪ ሥራ ማከናወን ። | | – | – | – |
| | – የ23 ከተሞች የዕቃዎችና አገልግሎቶች የችርቻሮ ዋጋ ጥናት:– | | | | |
| | • የ1983 መረጃ ሪፖርት ዝግጅት ። | – | | | |

| | | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት |
|---|---|---|---|---|---|
| የዋጋዎች ጥናት | • የ1984 መረጃ የኤዲቲንግና፣ኮዲንግ ፣ እንዲሁም የዳታ ኢንትሪ ሥራ ተጠናቆ ሪፖርት ዝግጅትና ሥርጭት ። | | — | — | — |
| | — በ89 ከተሞች የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ የዋጋ ጥናት:- | | | | |
| | • የ1983 ሪፖርት ማጠናቀቅ ። | — | | | |
| | • የ1984 መረጃ በየሩብ ዓመት የየወሩ ሪፖርት ዝግጅት | — | — | — | — |
| | — የአዲስ አበባ የዋጋ መመዘኛ/ኢንዴክስ/ዝግጅት /በየወሩ እየታተመ ለተጠቃሚዎች ይሠራጫል/ | — | — | — | — |
| የሕዝብ ጉዳይ ጥናቶች | — በ1976 የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ በተሰበሰበ መረጃ አዲስ በሚወጡ ተጨማሪ ሠንጠረዦችን በመጠቀም ጠለቅ ያለ ትንተና በልደት ፣ በሞት በፍልሰት በስራ ኃይልና በትምህርት ሁኔታ ላይ ማካሄድ ። | — | — | — | — |

..../ 46

4.4.2 /የቀጠለ/

| የጥናቱ ዓይነት | የሥራው ዓይነት | ሥራው የሚከናወንበት | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት |
| የሕዝብ ጉዳይ ጥናቶች | - የ1982 የወሊድና ቤተሰብ ጥናት ቅንብርና ሪፖርት ዝግጅት | | | | |
| | . የኢዲቲንግና ኮዲንግ ሥራ ማጠናቀቅ ፣ ከኮምፒውተር የሚወጡ ሠንጠረዦችን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ፣ | — | | | |
| | . መረጃውን መተንተንና ረቂቅ ሪፖርት ማዘጋጀት፣ | | — | — | |
| | . የመጨረሻ ደረጃ ሪፖርት ማዘጋጀትና ማውጣት ፣ | | | | — |
| | - የ1980 የቫይታል ስታቲስቲክስ ጥናት መረጃ ቅንብርና ሪፖርት ዝግጅት ፣ | — | — | — | — |
| | - የ1986 ሕዝብና ቤቶች ቆጠራ አስፈላጊው የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ይከናወናሉ:: ይኸውም ለቆጠራው የሚያስፈልጉ ማቴሪያሎች መጠይቆች ፣ መመሪያዎች ፣ ቅጾች ዝግጅት ፣ እንዲሁም የካርታ ሥራ ዝግጅትና የሙከራ ሥራዎች ማካሄድ፣ | — | — | — | — |
| የጊዜ አጠቃቀም የሙከራ ጥናት | - በሙከራ ጥናት የተሰበሰበው መረጃ ቅንብርና የሪፖርት ዝግጅት | — | — | | |

| | | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት |
|---|---|---|---|---|---|
| የጤና ጥናት /በገጠር/ | — በሁለት ዙሮች የሚካሄደው የጤና ጥናት የተሰበሰበው መረጃ የእርምት ፣ የኢዲቲንግና፣ ኮዲንግ ፣ የኮምፒውተር ቀንበርና የሠንጠረዦች ትክክለኛነት ማረጋገጥ ፣ | | — | — | — |
| ብሔራዊ የአመጋገብ ክትትል ሥርዓት ጥናት | — በሁለት ዙሮች የሚካሄደው ብሔራዊ የአመጋገብ ክትትል ሥርዓት ጥናት የተሰበሰበው መረጃ የኢዲቲንግና ኮዲንግ ፣ የኮምፒውተር ቀንበርና እርማት እንደዚሁም የሪፖርት ዝግጅት | — | — | — | — |
| የማህበራዊ ጉዳይ ጥናቶች | — ስለጤናና ሕግ ባለሙያዎች ማህበር መረጃዎች የሚሰበሰቡት መጠይቆችና መመሪያዎች ማጠናቀቅ ፣ | — | — | | |
| | . የተሰበሰቡትን መረጃዎች ማቀነባበር ፣ | | | | — |
| | — ስለሲኒማና ቲያትር ቤቶች የተሰበሰበውን መረጃ ማቀነባበር ሪፖርት ዝግጅት ፣ | — | — | — | — |
| | — ስለመምህራን ማህበር አባላት የተሰበሰበውን መረጃ ማቀነባበርና ሪፖርት ማዘጋጀት ፣ | — | — | — | |
| | — ስለቤተመጻሕፍት የሚሰበሰቡ መረጃዎችን ማቀነባበርና ሪፖርት ማዘጋጀት ፣ | | — | — | — |
| | — ሌሎች ተመሳሳይ ሥራዎችን የማቀነባበርና የማጠናቀቅ ተግባር ማከናወን ፣ | — | — | — | — |

4.4.2 /የቀጠለ/

| የጥናት ዓይነት | የሥራው ዓይነት | ሥራው የሚከናወንበት ጊዜ | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት |
| ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት ዝግጅት | — ለዓመታዊ ስታቲስቲክስ መጽሔት ዝግጅት ከተለያዩ መ/ቤቶችና ድርጅቶች የሚሰበሰቡ መረጃዎችና ከተለያዩ ጥናቶችና ቆጠራዎች ውጤት የተገኙ መረጃዎችን ለዚህ መጽሔት ዝግጅት በሚያመች ሁኔታ ማቀነባበር ። | — | — | — | — |
| ሌሎች ሥራዎች | — የአስተዳደር አካባቢዎችና ልዩ ልዩ ካርታዎች በተፈለገው መስፈርት ማዘጋጀት ። | — | — | — | — |
| | — ለልዩ ልዩ ጥናቶችና ሥራዎች የሚያገለግሉ መጠይቆች ፣ ሠንጠረዦች ፣ ግራፎች ፣ ቻርቶችና ጽሑፎች ማዘጋጀት ። | — | — | — | — |
| | — ለልዩ ልዩ መ/ቤቶችና ድርጅቶች አስፈላጊውን የቴክኒክና የማቴሪያል ድጋፍ ማድረግ ። | — | — | — | — |
| | — የአገር ውስጥና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ፣ እንዲሁም በአጠቃላይ የስታቲስቲክስ መረጃ ተጠቃሚዎች ለሚያቀርቡት የመረጃ ጥያቄ ምላሽ መስጠት ። | — | — | — | — |

...../49

| የሥራው ዓይነት | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት |
|---|---|---|---|---|
| በተለያዩ ምክንያቶች ሲተላለፍ የቆየው የግብርና ቆጠራ በ1985 እንደሚካሄድ ታሳቢ በማድረግ በ1984 በጀት ዓመት የቅድመ ዝግጅት ሥራዎችን ለማከናወን ታቅዷል:: ይኸውም የቅጾችና መመሪያዎች ዝግጅት ማጠናቀቅ ፣ የሕትመት ሥራ ፣ በቆጠራው የሚሳተፉ ሠራተኞች ምልመላና ሥልጠና ፣ የመስክ መገልገያ መሣሪያዎችን ማሟላትና ሌሎች አስፈላጊ ተግባራትን ማከናወን ፣ | — | — | — | — |
| በ1985 ለሚካሄዱ ቋሚና ሌሎች አዳዲስ ጥናቶች አስፈላጊ የሆኑ መጠይቆችና መመሪያዎች ማዘጋጀት ፣ ማባዛትና ማሠራጨት ፣ /የአከፋፋይ ንግድና የአገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ጥናት ፣ የቫይታል ስታቲስቲክስና የሰው ኃይል ጥናት /በገጠርና በከተማ/፣ የቤተሰብ በጀት ጥናት .....ወዘተ በቅድመ ዝግጅት ሥራው የሚጠቃለሉ ጥናቶች ናቸው/ | — | — | — | — |
| ባዲሱ ድርጅታዊ መዋቅር መሠረት የብሔራዊ የአካውንትሥራ በማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን አማካይነት የሚከናወን ሲሆን ሥራውን ለማስጀመር የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ይከናወናሉ:: ይኸውም ብሔራዊ አካውንትን በሚመለከት መሠረታዊ የሆኑ ሠንጠረዦች ማቀነባበርን የሚያጠቃልል ይሆናል:: | — | — | — | — |

......../ 50

4.4.3 / የቀጠለ/

| የሥራው ዓይነት | ሥራው የሚከናወንበት ጊዜ | | | |
|---|---|---|---|---|
| | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት |
| ከአለፈው የአሠራር ልምድ በመነሳት በ1985 ለሚካሄዱ ጥናቶች የአሠራር ዘዴዎችን ማሻሻልና የሌሎችን ሥራዎች የአሠራር ስልቶችን መቀየስ ፤ | – | – | – | – |
| ለስታቲስቲክስ መዝገብ አያያዝ የሙከራ ጥናት አስፈላጊው የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ማጠናቀቅ ፤ ስለሥራው ይዘትና የአሠራር ዘዴዎችን በመቀየስ በተመረጡ የኢኮኖሚ ዘርፎች የሙከራ ጥናት ለማካሄድ ባለሙያዎችን ማሠልጠንና በቂ ልምድ የሚያገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት ፤ | – | – | – | – |

ከዚህ በላይ በሠንጠረዥ እንደተመለከተው የ1983 እና የ1984 በጀት ዓመት የሰው ኃይል ለማነጻጸር እንዲያስችል ቀርቧል:: ሆኖም ለዕቅድ ዓመቱ የሚያስፈልገውን የሰው ኃይል በሙሉ ለማሟላት ተጨባጭ ሁኔታው ካለመፍቀዱም በላይ መሥሪያ ቤቱ ባለበት ከፍተኛ የቢሮ ጥበት ምክንያት የተጠቀሰው ተጨማሪ የሰው ኃይል ብቻ በማከል ሊቀርብ ችሏል:: የዕቅድ ዓመቱ የኮንትራት ሠራተኞች ብዛት ከ1983 ዕቅድ ዓመት ጋር ሲነጻፀር ዝቅ ብሎ ታይቷል:: ይኸውም በበጀት አጥረትና በተለያዩ ምክንያቶች በጥናቱ የሚሸፈኑ ገበሬ ማህበራት ብዛት እንዲቀነስ በመወሰኑ ነው:: በዕቅድ ዓመቱ ሠንጠረዥ ውስጥ ከታየው የኮንትራት ሠራተኞች ብዛት በተጨማሪ ለግብርና ጥናቶች በረዳትነት ከ800 በላይ ጊዜያዊ ሠራተኞች ለ60 ቀናት እንደሚቀጠሩ ይጠበቃል::

## 7. መወሰድ የሚኖርባቸው የፖሊሲና ድርጅታዊ አርምጃዎች፤

በአለፉት የእቅድ ዓመታት የተከሰቱት የአሠራርና የአፈጻጸም ችግሮች በሚቀጥሉት የእቅድ ዓመታት ተወግደው የአገሪቱ የስታቲስቲክስ ሥራ ግንባታ የጠበቀ መሠረት እንዲኖረው ለማድረግ በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ አስፈላጊው የፖሊሲና ድርጅታዊ እርምጃዎች መወሰድ ይኖርባቸዋል::

### 7.1 በመረጃ አሰጣጥና ዝግጅት የመሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች አለመተባበርና እምቢተኝነት ለማስወገድ እንዲቻል ባለሥልጣኑ የአስፈጻሚነት ኃይል እንዲኖረው ማድረግ፤

ስታቲስቲካዊ መረጃዎች የሚሰበሰቡት፤ ከናሙና ጥናቶች፤ ከቆጠራዎችና ከመዝገብት ላይ ስለሆነ የመሥሪያ ቤቶች፤ የድርጅቶችና የግለሰቦች ቀጥተኛና ትብብር እጅግ አስፈላጊ መሆኑ የሚታወቅ ነው:: በመሆኑም የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን የሚፈለገውን የስታቲስቲክስ መረጃ በጥራትና በወቅቱ ለመሰብሰብ የመረጃ ሰጪ አካላትን ትብብር ከመጠየቅና ሕጋዊ ግዴታቸው መሆኑን ከማሳሰብ አልፎ ብዙ ጊዜ በመመላለስ የሚባክነው ገንዘብ፤ ጊዜና የሰው ኃይል በቀላሉ የሚታይ አይደለም:: ይህም ሆኖ የመረጃ ሰጪ አካላት የሚያሳዩት ያለመተባበርና እምቢተኝነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመምጣቱ አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደርሷል:: ይህ ሁኔታ የልዩ ልዩ ስታቲስቲካዊ ሪፖርቶች መጽሔቶች ይዘት እንዲቀነስና በወቅቱ ለተጠቃሚዎች እንዳይሰራጩም ከፍተኛ ተጽዕኖ አድርጓል:: ለዚህም ዓይነተኛ ምክንያት መሥሪያ ቤቱ የተሰሚነትና የአስፈጻሚነት ኃይል ስለሌለውና በየዓመቱ በዚሁ ጉዳይ ላይ እርምጃ የማይወሰድ በመሆኑ ነው::

.../54

7.2 የአገሪቱ የስታቲስቲክስ ሥራ በማዕከላዊ አሠራር እንዲገነባ ማድረግ፣

በተለያዩ መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ልዩ ልዩ ስታቲስቲካዊ ሥራዎች በተናጠል የሚካሄዱ በመሆናቸው የሥራ መደጋገምና የሀገር ሀብት መባከንን የሚያስከትል ከመሆኑም በላይ የጽንሰ ሃሳብ፣ የአሠራር፣ የአመዳደብና የአተረጓጎም ተመሳሳይነት ስለሌለው የመረጃዎች ጥራትና ትክክለኛነት አጠያያቂ ከሚያደርገው ደረጃ ላይ አድርሷል:: ስለዚህ ይህን ሁኔታ ለማሻሻልና የስታቲስቲክስ ሥራዎች በማዕከላዊነት ባለው ሁኔታ ተግባራዊ እንዲሆኑ አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ ጠቃሚ ይሆናል::

በዚሁ መሠረት በሁሉም ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዘርፎች የሚከናወኑት ስታቲስቲካዊ ሥራዎች ባለሥልጣኑ ለብሔራዊ ስታቲስቲክስ ዕድገት የሚቀይሳቸውን የአሠራር ዘዴዎች ወይም ስልቶች እንዲከተሉ ለማድረግ የተቀናጀ የሥራ ግንኙነት በመሥሪያ ቤቶችና በድርጅቶች መካከል እንዲፈጠር ማድረግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል::

ለዚሁ ተግባራዊነት የስታቲስቲክስ መረጃ ተጠቃሚና አመንጭ ከሆኑት ከልዩ ልዩ መንግሥታዊና ሕዝባዊ ድርጅቶች ከተውጣጡ ባለሙያዎች የሚመሠረተው የብሔራዊ ስታቲስቲክስ አስተባባሪ ኮሚቴ ሥራዎችን የማስተባበርና የአገሪቱን የስታቲስቲክስ ሥራ ቀደም ተከተል የማውጣት ተግባር ስለሚኖረው በአስቸኳይ ተቋቁሞ ሥራውን መጀመር መቻል ይኖርበታል::

7.3 የባለሥልጣኑን የሠለጠነ የሰው ኃይል አጥረት ደረጃ በደረጃ ማስወገድ፣

ለአገሪቱ ስታቲስቲክስ ሥራ መሻሻልና መጎልበት የሠለጠነ የሰው ኃይል የሚጫወተው ሚና ከፍተኛና ወሳኝ እንደሆነ ይታወቃል:: በመሆኑም አዲሱን ድርጅታዊ መዋቅር ተግባራዊ በማድረግ ብሔራዊ የስታቲስቲክስ ሥራዎችን ለማስተባበር፣ ለመምራትና ለመቆጣጠር የሰለጠነ የሰው ኃይል በብቃት መገኘት ይኖርበታል:: በአሁኑ ወቅት የባለሥልጣኑን የሠለጠነ የሰው ኃይል ፍላጎት ሙሉ በሙሉ ለማሟላት የአገሪቱ አቅም የማይፈቅድ ቢሆንም ካለው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ ደረጃ በደረጃ ለማሟላት ይቻል ዘንድ ከወዲሁ ትኩረት ተደርጎበት አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ ጠቃሚ ይሆናል::

.../55

## 7.4 የቢሮ ጥበት ሁኔታን ማሻሻል፤

በመሥሪያ ቤቱ አማካይነት የሚከናወነው የስታቲስቲክስ ሥራና የሰው ኃይል በየጊዜው እየጨመረ እያደገ በመምጣቱ በተወሰኑ ቢሮዎችና የቦታ ይዞታ ለማስተናገድ ካለመቻሉም በላይ ሥራዎችንም በሚፈለገው ዓይነትና ፍጥነት ለማከናወን ከባድ ችግር እየፈጠረ ነው:: ይህ ችግር መፍትሔ እንዲያገኝ በማሰብ በ1980 የአቅድ ዘመን የሕንፃ ዲዛይን ሥራ የተጠናቀቀ መሆኑ ቢታወቅም የሕንፃው ሥራ በልዩ ልዩ ምክንያት በታሰበው ወቅት ሊከናወን ባለመቻሉ ችግሩ ተባብሶ ይገኛል:: ስለዚህ ይህ ችግር ከፍተኛ የሥራ እንቅፋት እንደሚሆን ታውቆ አስፈላጊው እርምጃ መወሰድ ይኖርበታል::